የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ሚያዚያ ቅጽ 1 ቁጥር 7

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ "ከገበሬው ቲቪ" የተሰኝ የቴሌቪዥን ጣቢያ ለመክፈት ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሰልጣን ፈቃድ አገኘ።

ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለ5 የሳተላይት ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ጣቢያ ለመጀመር ፈቃድ የጠየቁ ድርጅቶች ከቅድመ ማጣራት ሥራዎችን በኋላ ፈቃድ መስጠቱን በገለጸበት መግለጫ ላይ ድርጅቶቹ የፋይናንስ አቅምና ምንጫቸው ሥራውን ለማስኬድ አስተማማኝ መሆኑ፣ አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ድርጅታዊ አቅምና በፕሮጀክት ሰነዳቸው ያቀረቧቸው መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ብቁ መሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ፈቃድ መስጠቱን አስታውቋል።




ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ በዩቲዩብና ሌሎች የማኅበራዊ የትስስር ገጾች ኩባንያውን የተመለከቱ መረጃዎችን ሲያጋራ የቆየ ሲሆን ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ባገኘው ፈቃድ መሠረት ተደራሽነቱን ይበልጥ በማስፋት ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን የሚያስቃኙ መሰናዶዎችን ለተመልካች ለማድረስ በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጿል።

የቴሌቪዥን ጣቢያው በቀጣዮቹ ጥቂት ወራት ውስጥ ወደሥራ የሚገባ ሲሆን በሳምንት 7 ቀን ለ24 ሰዓታት በሚኖረው ሥርጭት በኩባንያው ከሚሠሩ የግብርናና ሌሎች ተግባራት በተጨማሪ በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚከናወኑ የግብርናና ተያያዥ ክንውኖች የሚዳስስ ይሆናል። ተፈጥሯዊ መስተጋብሮች፣ ከግብርና ጋር የተያያዙ ጠቃሚ መረጃዎችና አዳዲስ ፈጠራዎች በሚተዋወቁባቸው የጣቢያው ዝግጅቶችም የድርጅቱ ራእይ ማእከል የሆነውና የኢትዮጵያ ዋልታ ሆኖ የኖረው ገበሬ ሕይወት በልዩ ትኩረት ተደራሽ ይሆናል ተብሏል።

ከዚህ በተጨማሪም በግብርና የኢኮኖሚ ሽግግርን ለማምጣት የሚያስችሉ እና የግብርና ዘርፍ ፖሊሲዎችን ጨምሮ በርካታ ሃገራዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ መሰናዶዎችም በጣቢያው የሚቀርቡ ይሆናል።

ፐርፐዝብላክም በቅርቡ አስፈላጊውን ውል በመዋዋል ፈቃዱን ተቀብሎ ወደ ሥራ የሚገባ ሲሆን ድህነትን ታሪክ በማድረግ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንዲቻል እንዲሁም የጥቁር ሕዝብን ኢኮኖሚያዊ ልዕልና እውን ለማድረግ በሚሠራው ሰፊ ሥራ ሚዲያውን እንደአንድ መሳሪያ እንደሚጠቀም ተገልጿል።

ከዚህ ጋር ተያይዞም ኩባንያው ለመላው የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሠራተኞች፣ ባለአክሲዮኖች አጋር ድርጅቶችና ቤተሰቦች በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ በማለት ደስታውን ይገልጻል።

## በበዓላት የምናሳየው ኢኮኖሚያዊ መደጋገፍና ርሕራሄ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችንም ሊቀጥል ይገባል ሲሉ የፐርፐዝ ብላክ ኢትዮጵያ መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍሰሐ እሸቱ ገለጹ።

ዶ/ር ፍስሐ ይህንን ያሉት 1444 ኛውን የዒድ አል ፈጥር በዓል ምክንያት በማድረግ ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ባስተላለፉበት ወቅት ነው።

ምስል በ ኑበዮ ዳንኤል



> ❝
> **ዋና ሥራ አስፈጻሚው በመልእክታቸው "በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሶላትና ዘካ እንዲሁም ሰግደትና ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ስርዓቶች የሚደረጉበት የረመዳን ወር ማጠናቀቂያና ታላቅ በዓል የሆነው ኢድ አል ፈጥር ከታላላቅ የሙስሊም በዓላት መካከል አንዱ ሲሆን መላው ህዝበ ሙስሊም ከወዳጅ ዘመድ ጋር በመሆን በመብላትና በመጠጣት በደስታ የሚያሳልፈው፣ በመንፈሳዊ ትጋት ወደ አምላክ ከመቅረብ በኋላ ያለ የእውነተኛ ደስታ ምሳሌ በዓል ነው" ብለዋል።**

ኢድ አል ፈጥር ለሌሎች በማካፈልና በመተዛዘን የአብሮነት እሴት የሚጎለብትበት ታላቅ የፍቅር በዓል መሆኑን የገለጹት ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ከረመዳን ወር መጀመሪያ አንስቶ እስከ በዓሉ መቋጫ መላው የሙስሊም ማኅበረሰብ ከሌሎች ሀይማኖት ተከታዮች ጋር በመረዳዳት፣ በመተጋገዝ እና አብሮ ማእድ በመቁረስ ለዘመናት ያቆየውን የአብሮነት ባህል ለማጎልበት ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳበረከተ መዘንጋት የለበትም።

የረመዳን ፆም ወርም ከሌሎቹ ወራት በተለየ መልኩ ስጋን በመነሰም መንፈሳዊነት የሚለመልምበት፣ በጦምና ጸሎት ከታጀበ ምስጋና ጋር የሚደረግ ልግስናና የደግነት ወር መሆኑን ያስታወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው በእምነቱ አስተምህሮ መሸረት ህዝበ ሙስሊሙ ከመፆምና ከመስገድ ባሻገር ወሩን ሙሉ የተቸገሩትን በመርዳትና በጎ ሥራዎችን አብዝቶ በመተግበር ማሳለፉ ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር እባቶቻችን ጠብቀው ያቆዩአቸውን ኢትዮጵያዊ እሴቶች በማጠናከር ረገድ ያለው ሚና ላቅ ያለ ነው ብለዋል።

> "ሃገራችን በማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በታመሰችበት በዚህ ወቅት ከቤት ንብረታቸው፣ ተፈናቅለው በጊዜአዊ መጠለያ የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ፣ ወላጅ የሌላቸውን ልጆች በመርዳት እና ጧሪ ያጡ አረጋውያንን በመደገፍ ሊከበር ይገባል፣ በተለይ የተለያዩ ሃይላት በሐይማኖት ሽፋንና በቋንቋና በዘር ልዩነቶች ምክንያት ሊከፋፍሉን በሚታገሉበት በዚህ ጊዜ ምንም እድል ባለመስጠት ይልቁንም አንድነትና አብሮነታችንን ማጠናከርና አንደ ሃገር የጀመርነውን የልማት ጉዞ ማስቀጠል ያስፈልጋል።" ሲሉም መልእክአቸውን አስተላልፈዋል።

በመጨረሻም "ከብዙ ፈተናና ድካም በኋላ ደስታና በረከት አለ" ያሉት ዶ/ር ፍሰሃ እሸቱ እንደ ፈታኙ ቅዱስ የጦም ወር ረመዳንና እንደ ታላቁ የደስታ በአል ኢድ አል ፈጥር ተምሳሌት ለዘመናት ከነበሩና ጊዜ ካመጣቸው የግልና የጋራ ችግሮቻችን መታገል አብቅቶ የምናርፍበት፣ ተስፋ አስቆራጭ ከሆነውና ካደከመን ትግል የምናርፍበት ዘመን ሩቅ አይደለም፣ በረመዳን ወር በጦም እና ስግደት የደከመ ስጋ በፍቅር በሚቆረስ ማእድ በኢድ እንደሚጠግብ ሃገራችን በግጭቶች፣ መፈናቀሎች፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች የጎበጠችባቸው ቀናት አልፈው አዲስ የተስፋ ዘመን ይምጣልን በማለት መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

**TCTዝብላክ ግሎባል በሶማሊላንድ የሚጀምረው የTCTዝብላክ ሶማሊላንድ ቅርንጫፍ የአህጉሪቱን የኢኮኖሚ ልሕቀት እውን ለማድረግ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ተገለጸ።**

አጠቃላይ ግብርናን በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት በመላው የአፍሪካ አህጉር ኢኮኖሚያዊ ልማት አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን የሚያምነው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዘርፉን በመደገፍ አርሶአደሩን ተጠቃሚ ለማድረግና የኑሮ ውድነትን ታሪክ ለማድረግ ዓልሞ እየሠራ እንደሚገኝ ይታወቃል።

ፐርፐዝብላክ ግሎባል በኢትዮጵያ የጀመረውን ድህነትን ታሪክ የማድረግና የጥቁር ሕዝብን ልዕልና በቢዝነስ ሞዴል እውን የማድረግ ራዕይ በሌሎችም አገራት ተግባራዊ ለማድረግ በቅርቡ ፐርፐዝብላክ ናይጄሪያን ለማቋቋም እንቅስቃሴ መጀመሩ የሚታወስ ሲሆን ባሳለፍነው ሳምንት ደግሞ በሶማሌላንድ ፐርፐዝብላክ ሶማሊላንድ በሚል ስያሜ ተጨማሪ ቅርንጫፍ መክፈት የሚችልበትን የስምምነት ሰነድ ፊርማ ከሶማሊላንዱ ተወካይ አቶ ኢርሚያስ አድነው ጋር ተፈራርሟል።

Purpose Black ETHIOPIA

> በዕለቱ "እኛ አፍሪካውያን ከበቂ በላይ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት ሆነን ሳለ ያለንን ግብአት አጣምረን በጋራ መሥራት ባለመቻላችን መሠረታዊ ፍላጎቶቻችንን ሳይቀር በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆነን ለመጠበቅ ተገደናል፣ ሆኖም በራሳችን አቅም እና ጥረት ተደጋግፈን ከሠራን ስር ነቀል ለውጥ ማምጥት እንችላለን" በማለት ንግግር ያደረጉት የኩባንያው መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ "በማንኛውም የአፍሪካ አገር የሚቋቋመው TCTዝብላክ ተነሣሽነት ዋና ዓላማም የአገሪቱ ዜጎች ያለሌሎች ሃገራት እርዳታና ጣልቃ ገብነት በራሳቸው ጥረት ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ማስቻል ነው" ብለዋል።

እንደዋና ሥራ አስፈጻሚው ንግግር ፐርፐዝብላክ በቅርቡ በሶማሊላንድ የሚያስጀምረው ሥራ በኢትዮጵያ የታየው የተነሳሽነቱ ውጤታማነት በሌሎች የአህጉሪቱ አገራትም የገበሬዎችን ሕይወት ከመለወጥ፣ በአህጉራዊ ቀጠናው የጨመረውን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ከማቅለል ብሎም በኢኮኖሚ የዳበረ ማኅበረሰብን ከመፍጠር አኳያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ይኖረዋል።

እንቅስቃሴው ሶማሊላንድን ጨምሮ በሁሉም አገራት ከተወካዮች ወይም አስተባባሪዎች ጋር የጋራ ስምምነት ሰነድ በመፈራረም የሚጀምር ሲሆን መስራቾችን የማደራጀትና የተቋም መዋቅር እንዲኖረው የማስቻል ሥራዎች በቀጣይ የሚሠሩ እንደሚሆን ተነግሯል።

በየአገራቱ የሚመሠረተው የፐርፐዝብላክ ቅርንጫፍ በዋናነት ከ70 በመቶ በላይ የሆነው የአህጉሪቱ ሕዝብ ጥገኛ በሆነበት ግብርና እና በየአገሪቱ ባሉ አዋጭ የልማት አቅጣጫዎች ላይ በማተኮር የግብርና ማቀነባበሪያና ተያያዥ ሥራዎች ላይ የሚሰማራ ሲሆን በርካታ ዜጎች ራሳቸውን እንዲችሉ ሰፊ የሥራ ዕድልን እንደሚፈጥርም ይጠበቃል ተብሏል።

ፐርፐዝብላክ ሶማሊላንድ በኢትዮጵያና ሶማሊላንድ መካከል እንዲሁም በአህጉር አቀፍ ደረጃም የጠበቀ የንግድ ትስስርን ከመፍጠር ባሻገር ጥቁሮች በራሳቸው የጋራ ጥረት ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅምን እንዲያዳብሩ የሚያስችል ሲሆን በአገራቱ መካከል የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን በመፍጠር ረገድም አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ተገልጿል።

**ውስን የሆኑ የእርሻ ምርቶችን ብቻ ከማምረት ይልቅ የእርሻና የእንስሳት እርባታን በጥምረት መሥራት ይበልጥ ትርፋማ እንደሚያደርግ ተገለጸ።**

ከአንድ ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮችን ባለአክሲዮን ለማድረግ እና የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲኾኑ ለማስቻል 7 ማስተባበሪያና 10 ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ከፍቶ እየሠራ የሚገኘው ከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር የተለያዩ ዓይነት አዝርእት፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ልማት ከዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ጋር በማዋሐድ ለመሥራት በዝግጅት ላይ መሆኑን የፐርፐዝብላክ ቺፍ ቴክኒካል ኦፐሬሽን ኦፊሰር አቶ አስናቀ ኃ/ሚካኤል ገልጸዋል።

በተቀናጀ የግብርና አሠራር ከግብርና ውጤቶች የሚገኝ ተረፈ ምርትን ለእንስሳት መኖ ማድረግ የእንስሳቱን ፍግ ደግሞ ለእርሻ መሬት ማዳበሪያነት መጠቀምን እንደምሳሌ ያነሡት ኃላፊው ሁሉንም የግብርና ዘርፎች ተደጋግፈው እንዲከወኑ በሚያስችል አሠራር ላይ መሠማራት ይበልጥ አመርቂ ውጤት ማስገኘት መቻሉንም አብራርተዋል።

ከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐ ግብር እስካሁን ባከናወናቸው የቅርንጫፍ ቢሮዎች ማቋቋም እና የግብርና ተግባራት አመርቂ ውጤቶችን እንዳስመዘገበ የገለጹት ኦፐሬሽን ኦፊሰሩ በቀጣይም በግብርናው ዘርፍ የብዙ ዓመት ልምድን ባካበቱ ባለሙያዎችና በጥናት በተረጋገጡ ሳይንሳዊ ግኝቶች እንዲሁም ዘመናዊ የግብርና መሣሪያዎች በመታገዝ የግብርና ሥራውን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ኩባንያው በፍራንቻይዝ ሞዴል ከሚያከናውናቸው ውጤታማ የግብርና እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ ባስሚን ሞደርን ፖሊተሪ ፋርም ከተባለ ድርጅት ጋር በመቀናጀት የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች እርባታ ሊጀምር መሆኑንም አስታውሰዋል።

> “
>
> **“በርካታ የአረብ ሃገራት እጅግ ደረቅ እና ሞቃታማ የሆነ የአየር ንብረታቸው ከአሸዋማ መሬታቸው ጋር ተደምሮ የእርሻ ሥራን ከባድ ሊያደርገው ቢችልም እጅግ ዘመናዊ በሆነ ዘዴ በአይነትና በብዛታቸው ብዙ የሆኑ የግብርና፣ የእንስሳት እና የማቀነባበሪያ ውጤቶችን ከራሳቸው ምግብ ፍጆታ ተርፎ ለዓለም ገበያ በገፍ ያቀርባሉ።” ያሉት ኀላፊው “እንደ ኢትዮጵያ ባለ ምቹ የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት ባላት አገር ሰፊና ባዶ መሬቶችን ማልማት አቅቶን መራብ አይገባንም” ሲሉ በአጽንዖት ተናግረዋል።**

ኃላፊው ዘርፉን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ሊሠራባቸው የሚገቡ አቅጣጫዎችን ለግለሰቦችም ሆነ ለመንግሥት መጠቆም፣ በዘርፉ የተሠማሩ ሥራ ፈጣሪዎችን ማበረታታት እና በከተማም ሆነ በገጠሩ የአገራችን ክፍል ዜጎችን አደራጅቶ ማሰማራት በግብርናው ዘርፍ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ወሳኝነት አለው ያሉ ሲሆን ከልማዳዊ የአስተራረስ ዘዴ በመላቀቅም ለጥራጥሬዎች እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎች ተስማሚ የአየር ንብረት እና የመሬት አቀማመጥ መርጦ ማልማት ለምርታማነት መጨመር ትልቅ አስተዋጽዖ አለው ብለዋል።

በመጨረሻም በአንድ የእርሻ መሬት ላይ የሚደረግን የአንድ አይነት ምርት እና ተደጋጋሚ እርሻ እንደ አንድ ማነቆ ያነሱት አቶ አስናቀ ከመጠን ያለፈ ምርትን ከገበያው ፍላጎት ውጪ አምርቶ ለብልሽት ከመዳረግ በማንኛውም ጊዜ በቂ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ግብርናውን ወቅትን ጠብቆ ከማረስ ለማላቀቅ ፕርፕዝብላክ በግብርና ክፍሉ በትኩረት እየሰራ ነው ያሉ ሲሆን የኩባንያው አግሮፕሮሰሲንግ ክፍልም የግብርና ምርቶችን ከብልሽት ለማዳንና ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ለማድረግ ትልልቅ ማቀነባበሪያዎችን ገንብቶ ወደስራ ለመግባት በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑን አስታውሰዋል።

ይህም ተፈጥሯዊ ይዘታቸውን የጠበቁና ጤናማ ምግብ ነክ ነገሮችን ለሃገር ውስጥ ገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የሚያስችል ሲሆን እንደሃገር በምግብ ራስን የመቻል ሕልም እውን ለማድረግና አካባቢን ከመጠበቅ አንጻር ትልቅ ሚና ይኖረዋል ተብሏል።

KIEP
KEGEBEREW INTEGRATED EXPANSION PROGRAM

**ፕርፕዝብላክ ኢቲኤች ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ጋር አብሮ መሥራት በሚችልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ፍሬያማ ውይይት አካሔደ።**

የጥቁርን ሕዝብ ሁለንተናዊ ልማት እና ኢኮኖሚያዊ እድገት እውን ለማድረግ ልዩ ልዩ የቢዝነስ ሞዴሎች ላይ ተሠማርቶ የሚገኘው ፕርፕዝብላክ ኢትዮጵያ ከተለያዩ መንግሥታዊ እና የግል ተቋማት ጋር እንቅስቃሴዎቹን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችሉትን ሥራዎች እያከናወነ እንደሚገኝ የሚታወስ ሲሆን ባሳለፍነው ሳምንትም ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ጋር ፍሬያማ ውይይት ማድረጉ ተገልጿል።

በውይይቱ የኩባያውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱን ጨምሮ የፕርፕዝብላክ የሥራ አመራር አባላት የተገኙ ሲሆን የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንደተገኙበት ለማወቅ ተችሏል።

ከተለያዩ ኢንቨስተሮች ካፒታልን በዓይነትና በብዛት በማሰባሰብ መልሶ ካፒታልን ለሚፈልጉ ድርጅቶች እና ለመንግሥት ለተለያዩ አዋጭ ፕሮጀክቶችና የንግድ ሐሳቦች እንዲያወጡት የሚያመቻች የገበያ ሥርዓት የሆነው ካፒታል ገበያ እንደ ፕርፕዝ ብላክ ኢትዮጵያ ያሉ ትልልቅ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ይዘው ወደገበያ ለሚገቡ ድርጅቶች እና በኢንቨስትመንት ተሳትፎ ለሚኖራቸው ሁሉ የተመቻቸ መገበያያ መንገድ እንዲኖር ዓይነተኛ ሚና እንደሚኖረው በውይይቱ ተነሥቷል።

ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ የድርጅቶችን ሰነዶችና የባለቤትነት መብት በቀላሉ መግዛትና መሸጥ ማስቻሉ በአገር አቀፍ ደረጃ ኢንቨስትመንትንና ቁጠባን የሚበረታታው የካፒታል ገበያ ፕርፕዝብላክ ኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች ለመሳተፍ እንዲችል እና በተሰማራባቸው ዘርፎች ጉልህ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ማስመዝገብ እንዲችል እንደሚያግዘውም ነው በተከናወነው ውይይት ላይ የተገለጸው።

በተጨማሪም የካፒታል ገበያ ሥርዓት ለኢንቨስትመንት ባንኪንግ ሴክተሩ መሻሻል የዉጭ ምንዛሬ የማግኘት አቅማችን እንደአገር ከፍ የሚያደርግ እና ምንአልባትም ኤክስፖርት የማድረግ አቅማችንን እንደሚሳድግ የተነሣ ሲሆን እንደ ፕርፕዝብላክ ያሉ በአገር ዉስጥ የሚመሰረቱ ግዙፍ የማምረቻ ድርጅቶች በግብርና እና ሌሎችም ዘርፎች የዉጭ ብድር የማግኘት አቅማቸው እንዲያድግ እንደሚያደርግ ተገልጿል፡፡

ምስል በ ኤደን ደነቀ



**ዋና አዘጋጅ፡ ሰላማዊት ደበበ**
**ሲንየር ሪፖርተር፡ ጌታባለው ገ/ሐና**
**ሪፖርተር፡ ኤደን ደነቀ**

**ለበለጠ መረጃ**

ስንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com